# <u>ለወገን ደራሽ ወገን በመሆንም የእርዳታ እና የትብብር ጥሪ — አምባ (የአማራ ባለሞያዎች ማህበር)</u>





አበጥር ወርቁ የ14 ዓመት ታዳጊ ነው። እስከ ቅርብ ጋዜ እንደማንኛውም ታዳጊ ብሩህ ተስፋ ነበረው። አበጥር ተወልዶ ባደገበት መተከል (የአሁኑ "ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል") በጉሙዝ ብሄረሰብ ተወላጆች አማራ ስለሆነ ብቻ ለህሊና በሚዘገንን መልኩ ብልቱ ተሰልቦ፣ አይኑ ተጎልጉሎ፣ ፊቱና አካሉ በስለት ተተልትሎ በሞትና በህይዎት መካከል ሆኖ ተስፋው እስከ ወዲያኛው እንዳይጨልም እየታገለ ይገኛል። የዚህ ታዳጊ ዘግናኝ ጉዳት በበርካታ አማራ ወገኖቻችን ላይ የደረሰውንና እየደረሰ ያለውን ግፍ ፍንትው አድርጎ ያሳያል። በአሁኑ ወቅት በርካታ የአማራ ተወላጆች ያለ ምንም ምክንያት ተወልደው ካደጉበት ቀየ "መጤ" ተብለው ንብረታቸውን እየተዘረፉ እየተሰደዱ ሲሆን እሚደርስላቸው ወገን፣ አቤት እሚልላቸው አካል ይፈልጋሉ።

አበጥር በአሁኑ ሰዓት በባህዳር ህክምና እየተደረገለት ሲገኝ፣ ከተለያዩ "ክልሎች" "መጤ" ተብለው የተሰደዱ የአማራ ተወላጆች ደግሞ ገሚሶቹ በቤተ ክርስቲያን ገሚሶቹ ደግሞ መጠጊያ አጥተው ጎዳና ላይ ወድቀዋል።

ይህ ግፍ እንዲቆም አማራና የአማራ ወዳጅ ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲጮሁላቸው፣ በፀሎታቸው እንዲያስቧቸው፣ በተቻላቸው አቅም ሁሉ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው አምባ የአማራ ባለሞያዎች ማህበር አበክሮ ይጠይቃል።

አምባ የሚሰበሰበውን ገንዘብ አበጥርንና ቤተሰቦቹን ለመርዳት እና በግፍ "መጤ" ተብለው ከትውልድ ቦታቸው የተፈናቀሉ አማሮችን ለማቋቋሚያ ያውላል።

የአማራ ባለሞያዎች ማህበር (አምባ) ወገኖቻችን ለመርዳት እያደረገ ያለውን የገዘብ እርዳታ ማሰባሰብ ለማገዝ GOFUNDMe ከዚህ ላይ የበኩልዎትን ማድረግ ይችላሉ።

https://www.gofundme.com/save-abetir-w-help-displaced-amara

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**
**አምባ የአማራ ባለሞያዎች ማህበር**